# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ROCKVILLE, MARYLAND

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፍትሃዊ ተጠያቂነት አርአያ/ሞዴል

# የፍትሃዊነት ተጠያቂነት/ሀላፊነት አርአያ/ሞዴል

የ MCPS የፍትሃዊነት ተጠያቂነት/ሀላፊነት አርአያ/ሞዴል* የትምህርት ቤት ስኬታማነትን በተመለከተ ዝርዝር እና ትኩረት ያለው ምዘና ይሰጣል፣ እንዲሁም የሁሉንም ተማሪዎች አፈጻጸም በይፋ እየተከታተለ ሪፖርት ያደርጋል። የ MCPS ተገቢነት፣ ትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት-ተጠያቂነት/ሀላፊነት አርአያ አይነት ከተለመደው አይነት የስቴት እና የፌደራል ጅምላ የሪፖርት አቀራረብ ባለፈ መልኩ/ባሻገር ተመሣሣይ/እኩል ተደራሽ እድል ወይም እንደሌሎች ስኬታማ የመሆን እድል ባላገኙት የተማሪዎች ትኩረት ቡድን ላይ በዝርዝር ሪፖርት የማድረግ ሥራ ይሠራል።

የሁሉም ተማሪዎች የአፈጻጸም ክትትል የሚደረግ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለአምስት የትኩረት ቡድኖች ትክክለኛ/ሚዛናዊ-ተጠያቂነት ነጥብ ይመደባል።

| የትኩረት ቡድኖች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Non-FARMS<br>ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ | Non-FARMS<br>ሂስፓኒክ/ላቲኖ | FARMS<br>ነጭ/ኤዥያውያን/ሌሎች አጠቃላይ የተማሪ ቡድኖች | FARMS<br>ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ | FARMS<br>ሂስፓኒክ/ላቲኖ |

## የትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት-ተጠያቂነት ሞዴል ለምንድነው የተገነባው?

ስቴቱ ለፐብሊክ ስኩልስ ትክክለኛ እና ጥብቅ የሆነ የትምህርት መስፈርቶችን ማቋቋም/መመስረት ቢኖርበትም፣ ትምህርት በመሠረታዊነት የአካባቢ ኃላፊነት በመሆኑ እና በአካባቢ ደረጃ የሚተዳደር ነው። ህብረተሰቡ በትምህርት ስርዓት ላይ ያለውን እምነት ለማስጠበቅ እና ለት/ቤቶች ዲስትሪክት ልዩ የሆኑ ግቦችን ለማሳካት የ MCPS የመቆጣጠር እና ሪፖርት የማድረግ ብቃትን ለማስጠበቅ በሚፈለገው ሁኔታ የተዘጋጀ የ MCPS የፍትሃዊነት ተጠያቂነት/ሀላፊነት አርአያ/ሞዴል አስፈላጊ ነው።

### የትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት-ተጠያቂነት ሞዴሎች ክፍለ አካላት

የትክክለኛነት፣ ሚዛናዊነት-ተጠያቂነት ሞዴሎች የተለያዩ ክፍሎች በየጊዜው በሚገኙ መረጃዎች/ዳታዎች መሰረት በተለያዩ ጊዜያት ይለቀቃሉ። መረጃዎች የሚለቀቁበት የጊዜ ሠሌዳ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- የትምህርት ውጤት
- የምረቃ መጠን
- አካዴሚያዊ ግስጋሴ
- የእንግሊዝኛ ችሎታ ውስንነት
- ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች
- ባህልና ፍትህ
- ቅድሚያ ትኩረት

*ስለ ውጤታማነት፣ ግስጋሴ፣ ምረቃ እና የአካል ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች/የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች 2018-2019 የትምህርት ዓመት ፍትሀዊ ኃላፊነት የተሞላበት ሞዴል የሪፖርት አቀራረብ።

# የትምህርት ውጤት**

የትምህርት ውጤታማነት አንዱ ዓይነት የ MCPS ፍትሃዊ ሃላፊነት/ተጠያቂነት ሞዴል ነው። የትምህርት ስኬታማነት የሚያተኩረው በተማሪ አፈፃፀም በርካታ የትምህርት አሰጣጥ መሰረታዊ ማስረጃ መስፈርቶች ማዕቀፍ ላይ ተመስርቶ ነው።

| ስለ ስኬታማነት ሪፖርት ክትትል የሚያደርግ ቡድን | ደረጃ የጠበቀ የስኬት አካል | የትኩረት ቡድኖች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፋርምስ - ያልሆነ (Non-FARMS) ነጭ/ ኤዥያዊ/የሌላ ተማሪ ቡድኖች በሙሉ | 90% ወይም የበለጠ | Non-FARMS ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ | Non-FARMS ሂስፓኒክ/ላቲኖ | FARMS ነጭ/ ኤዥያውያን/ሌሎች አጠቃላይ የተማሪ ቡድኖች | FARMS ጥቁር ወይም አፍሪካዊ አሜሪካዊ | FARMS ሂስፓኒክ/ላቲኖ |

** ከሶስት ሁለቱን የመማር መስፈርት ፈርጆች/ምድቦች ማረጋገጫ ያሟሉ ተማሪዎችን ቁጥር እና በመቶኛ ሪፖርት ማድረግ።

## MCPS ፍትሃዊ ተጠያቂነት ምሳሌ ናሙና ዘገባ፡-

### የስኬት አካል (School A)

ቀጥሎ ያለው የትምህርት/አካደሚክ ስኬታማነት አካል ናሙና የትምህርት ቤት ሪፖርት ነው። ነጥብ አሰጣጡ በተለዩ የትኩረት ቡድኖች ውስጥ ባሉ የተማሪዎች አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ ነው። የተቀመጠውን መለኪያ ነጥብ ለሚያሟሉ የትኩረት ቡድኑ ተማሪዎች መቶኛ ነጥብ ይሰጣል (Key to EOL Assigned Score ይመልከቱ)። የትምህርት ቤቱን የአካዳሚያዊ ስኬት ውጤትን የሚወክለዉ፣ የተመደበው ዉጤት አማካይ በመጨረሻው አምድ ውስጥ ተካትቷል።

| | Non-FARMS ሌሎች አጠቃላይ የተማሪ ቡድኖች | የትኩረት ቡድኖች: Non-FARMS ጥቁር ወይም አፍሪካዊ - አሜሪካዊ | Non-FARMS ሂስፓኒክ/ላቲኖ | FARMS ሌሎች አጠቃላይ የተማሪ ቡድኖች | FARMS ጥቁር ወይም አፍሪካዊ - አሜሪካዊ | FARMS ሂስፓኒክ/ላቲኖ | የትኩረት ነጥብ/ግብ: የትምህርት ስኬት ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የማንበብ/መጻፍ ውጤት | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2.4 |
| የማንበብና የመጻፍ ውጤት በመቶኛ | 90.3 | 84.4 | 71.4 | 57.1 | 56.3 | 62.6 | |
| | | | | | | | |
| የሒሳብ ውጤት | 3 | 2 | 2 | 1 | 0 | 0 | 1 |
| የሒሳብ ውጤት በመቶኛ | 80.6 | 68.9 | 51.4 | 47.6 | 33.3 | 30.8 | |

**ለ EOL የተሰየመ ውጤት የመፍቻ ቁልፍ**

- 4 ትኩረት የተጣለባቸው ተማሪዎች ያገኙት ≥90%
- 3 ትኩረት የተጣለባቸው ተማሪዎች ያገኙት 70-89%
- 2 ትኩረት የተጣለባቸው ተማሪዎች ያገኙት 50-69%
- 1 ትኩረት የተጣለባቸው ተማሪዎች ያገኙት 35-49%
- 0 ትኩረት የተጣለባቸው ተማሪዎች ያገኙት 0-34%